# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ማህበራት መቋቋሚያና መተዳደሪያ መመሪያ ቁጥር 12/2015

2015

አዲስ አበባ

# 1. መግቢያ

2. የሀገራችን ስፖርት በተለያዩ ጊዜያት በአደረጃጀትና በአመራር መዋቅሮች ህዝብ በቁጥር የሚያዳግቱ ውስብስብ ችግሮች ያለፈ እና የነበረ መሆኑ ይታወቃል፣ በዚህ መሰርፈት የኤ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት በስፖርቱ ዘርፍ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ለመጀመሪያ ጊዜ በ1990 ዓ.ም የስፖርት ፖሊሲ በሚኒስቴሮች ምክር ቤት የፀደቀ ሲሆን ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስታዊና ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶች በአደረጃጀታቸው በመዋቅር ተጠናክረው የተሰጣቸውን እየተወጡ ይገኛል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግከፀደቀበት ጀምሮ በቀጥታ ስፖርቱን የሚወክሉ መንግስታዊ መዋቅሮችን ከከተማ እስከ ወረዳ ድረስ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እንዲሁም ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶችን በከተማ፣ በክ/ከተማ፣ በወረዳ ደረጃ ምክር ቤቶችን፣ ፌዴሬሽኖችን፣ አሶሴሽኖችንና የስፖርት ኮሚቴዎችን በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች በማቋቋምና ስራ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ነው፡፡ ሆኖም ግን መዋቅሮች በአደረጃጀታቸው የተጠናከሩ ቢሆኑም ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶች **ከ1995ዓ.ም እስከ 1997ዓ.ም** ጀምሮ የተለያዩ መቋቋሚያና መተዳደሪያ መመሪያዎች ወጥቶላቸው ቢደራጁም የተጠበቀውን ውጤትና የከተማውን ህብረተሰብ የስፖርት ፍላጎት አገልግሎት በመስጠት አርክተዋል ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ከ1997 - 2003**ዓ.ም** ድረስ ወጣቶችና ስፖርት በቢሮ ደረጃ የተደራጀ ሲሆን በመቀጠልም **ከህዳር** 2003-**ህዳር** 2008**ዓ.ም** ጀምሮ በኮሚሽን ደረጃ ሆኖ **ከህዳር** 2008 - 2010**ዓ/ም** ጀምሮ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በሚል መጠሪያ ሲጠቀም ቆይቶ በ2011ዓ/ም **የአዲስ አበባ ስፖርት ኮሚሽን** በአዲስ መልክ ተዋቅሯል፡፡ ቀደም ሲል የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የነበረው መዋቅራዊ አደረጃጀት የወጣቱንና የስፖርቱን ስራ በአንድ ላይ አጣምሮ ይዞ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር ----/201-- በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ደረጃ በአዲስ መልክ ተደራጅቷል፡፡
3. ይህንን ተከትሎ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ም/ቤት የስፖርት ማህበራትን የማቋቋምና የማደራጀት ስልጣን በተሰጠው መሰረት የከተማዋን ሕዝባዊ ስፖርት አደረጃጀት ከቀደሙት ችግሮች በመነሳት ጥራት ያለው፣ ወጥ የሆነ ተጠያቂነትና ግልፅነት ያለበት እንዲሁም የባለቤትነት ስሜት በመፍጠር በአሰራርና በአተገባበር ተስማሚ የሆነ የስፖርት ማህበራት መቋቋሚያና መተዳደርያ መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

4. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በአዋጅ **ቁጥር ----/201-----** በተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት መሰረት የአዲስ አበባ ስፖርት ምክር ቤት ይህንን የስፖርት ማህበራት ፌደሬሽኖች መቋቋሚያና መተዳደርያ መመሪያ አውጥቷል፡፡

5. **አጭር ርዕስ፤**

ይህ መመሪያ **የአዲስ አበባ ስፖርት ማህበራት መቋቋሚያና መተዳደሪያ መመሪያ** ቁጥር 008/2014 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

5.1. **ትርጓሜ፡**

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

5.1.1. "**ስፖርት**"፦ ማለት በኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ መሰረት ማንኛውም ግለሰብ አቅሙ በፈቀደ መጠን በግሉ ወይም በጋራ በተደራጀና ባልተደራጀ መልክ የሚከናወኑ የተለያዩ የአካል እንቅስቃሴዎች ሆኖ የስፖርት ስልጠናዎችንና ውድድሮችን ያጠቃልላል፡፡

5.1.2. "**የከተማ አስተዳደር**"፦ ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

5.1.3. "**ቢሮ**" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርቱን በበላይነት እንዲመራ በአዋጅ ስልጣን የተሰጠው ተቋም ማለት፡፡

5.1.4. "**ስፖርት ምክር ቤት**"፦ ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በመመሪያ ቁጥር 007/2014 የተቋቋመ ም/ቤት ነው፡፡

5.1.5. "**የስፖርት ማህበር**"፦ ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እውቅና አግኝቶ በፌዴሬሽን፣ በአደራጅ ኮሚቴ፣ በስፖርት ኮሚቴ፣ በአሶሴሽን ደረጃ የተቋቋመና አንድን ስፖርት በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ለመምራትና ለማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጠው የስፖርት ማህበር ነው፡፡

5.1.6. "**ፌዴሬሽን**" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እውቅና አግኝቶ የተቋቋመና አንድን ስፖርት በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ለመምራትና ለማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጠው የስፖርት ማህበር ነው

5.1.7. "**የስፖርት ኮሚቴ**" ማለት አንድን የስፖርት ዓይነት ከአንድ በላይ የስፖርት ዓይነቶችን በወከሉት የህብረተሰብ ክፍል ለማስፋፋት፣ ለመምራት፣ ለማስፈፀምና አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ የስፖርት ማህበር ነው፡፡

5.1.8. "**የስፖርት አደራጅ ኮሚቴ**" ማለት አንድ ስፖርት ለመምራት የፌዴሬሽንን አቅም እስኪያሟላ ድረስ የተቋቋመ የስፖርት ማህበር ነው፡፡

5.1.9. "**የስፖርት አሶሴሽን**"፦ ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እውቅና አግኝቶ በተቋቋመበት የስፖርት ዓይነት በከተማ አስተዳደሩ ለመምራትና ለማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጠው የስፖርት ማህበር ነው፡፡

5.1.10. "**የስፖርት ክለብ**"፦ ማለት የስፖርት እንቅስቃሴን ለማራመድ በአዲስ አበባ ስፖርት ኮሚሽን እውቅና አግኝቶ የተቋቋመ የስፖርት ቡድን ነው፡፡

5.1.11. "**አባላት**"፦ ማለት የስፖርት ምክር ቤት አባል የሆነና በስፖርት ማህበራት የታወቁ የስፖርት ድርጅቶች ተወካይ ግለሰቦች ናቸው፡፡

5.2. “**ዓቃቢ ነዋይ**”፦ ማለት በስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ የፌዴሬሽኑ ንብረትና ገንዘብ የሚከታተልና የሂሳብ እንቅስቃሴ የሚቆጣጠር የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ነው፤

5.3. “**አባል**”፦ ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ አባል እንዲሆን ተቀባይነት ያገኘ አካል ነው፡፡

5.4. “**ሰው**”፦ ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

5.5. “**ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ**”፦ ማለት አንድን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ማህበርን ለመምራት በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥና ስፖርት ማህበሩን ሥራ በበላይነት የሚያስፈፅም አካል ነው፡፡

## 6. የስፖርት ማህበሩ ዓላማ፤

6.1. በአደስ አበባ ከተማ በቀጥታ የተወከለበትን ስፖርት በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲታወቅና እንዲስፋፋ ማድረግ፤

6.2. በወከለው የስፖርት ዓይነት የአቅም ግንባታ፣ የስፖርት ስልጠናዎችን እንዲሰጥና ውድድሮችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በማካሄድ ተተኪ ምርጥ ስፖርተኞችን ማፍራት፣

6.3. በሚወክለው የስፖርት ዓይነት በከተማ፣ በክ/ከተማና በወረዳ ደረጃ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር የተጠናከረ ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቱን ማጎልበት፤

6.4. በስፖርቱ የሚወጡ ዓለም አቀፋዊ፣ ክፍለ አህጉራዊ፣ አገር አቀፍና ከተማ አቀፍ ደንቦችና መመሪያዎች በከተማ ውስጥ እንዲታወቅና እንዲሰራባቸው ማድረግ፣

## 7. ከተማ አቀፍ የስፖርት ማህበር ስለማቋቋም፤

7.1. **አንድ ከተማ አቀፍ** የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ **መመስረት የሚቻለው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፦**

7.1.1. ቢያንስ በ6 ክፍለ ከተሞች ፌዴሬሽን፣ መደራጀቱ ሲረጋገጥ

7.1.2. በቡድን ስፖርቶች 5 ክለቦች ተደራጅተው መኖራቸዉ ሲረጋገጥ ነው፤

7.1.3. በግል ስፖርቶች በክፍለ ከተማ የተመዘገቡ ቢያንስ 150 ስፖርተኞች ሲኖራቸው፤

7.1.4. በአርት ስፖርቶች ቢያንስ በ2ኛ ዲን ደረጃ የሚያሰለጥኑ 5 የስልጠና ማዕከላት በክፍለ ከተማ ሲኖራቸው፤

7.1.5. በክፍለ ከተማ ደረጃ የተመዘገቡ ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ያላቸው ቢያንስ 15 አሰልጣኞችና 15 ዳኞች መኖራቸው ሲረጋገጥ፣

7.1.6. በክፍለ ከተማ ደረጃ ስፖርቱ የሚዘወተርባቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በኪራይና በትውስት መኖራቸው ሲረጋገጥ ፣

7.1.7. የስፖርት ማህበሩ ለመቋቋም አምስት የክፍለ ከተማ ስፖርት ኮሚቴዎችና ክለቦች ወይም ፅ/ቤት ሲያረጋግጡ፤

7.1.8. በስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ማቅረብ ሲችል፡፡

7.1.9. የሂሳብ አያያዝን ሥርዓት የዘረጋ እና ኦዲትን በስራ ሊይ የሚያውል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

7.1.10. ፅህፈት ቤት እና የሰዉ ሀይል መኖሩ ሲረጋገጥ

7.2. **አንድ ከተማ አቀፍ የስፖርት አሶሴሽን መመስረት የሚቻለው ከዚህ በታቾ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡-**

7.2.1. ቢያንስ በ6 ክፍለ ከተሞች አሶሴሽን መደራጀቱ ሲረጋገጥ

7.2.2. በቡድን ስፖርቶች 5 ክለቦች ተደራጅተው መኖራቸዉ ሲረጋገጥ ነው፤

7.2.3. በግል ስፖርቶች በክፍለ ከተማ የተመዘገቡ ቢያንስ 150 ስፖርተኞች ሲኖራቸው፤

7.2.4. በአርት ስፖርቶች ቢያንስ በ2ኛ ዲን ደረጃ የሚያሰለጥኑ 5 የስልጠና ማዕከላት በክፍለ ከተማ ሲኖራቸው፤

7.2.5. በክፍለ ከተማ ደረጃ የተመዘገቡ ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ያላቸው ቢያንስ 15 አሰልጣኞችና 15 ዳኞች መኖራቸው ሲረጋገጥ፣

7.2.6. በክፍለ ከተማ ደረጃ ስፖርቱ የሚዘወተርባቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በኪራይና በትውስት መኖራቸው ሲረጋገጥ ፣

7.2.7. የስፖርት ማህበሩ ለመቋቋም አምስት የክፍለ ከተማ ስፖርት ኮሚቴዎችና ክለቦች ወይም ፅ/ቤት ሲያረጋግጡ፤

7.2.8. በስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ማቅረብ ሲችል፡፡

7.2.9. የሂሳብ አያያዝን ሥርዓት የዘረጋ እና ኦዲትን በስራ ሊይ የሚያውል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

7.2.10. ፅህፈት ቤት እና የሰዉ ሀይል መኖሩ ሲረጋገጥ

7.3. **አንድ ከተማ አቀፍ የስፖርት አደራጅ ኮሚቴ መመስረት የሚቻለው ከዚህ በታቾ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡-**

7.3.1. ስፖርቱ በክፍለ ከተሞችና በቡድኖች በድምሩ 3 ቡድኖች ተደራጅተው መዘውተሩ ሲረጋገጥ ነው፤

7.3.2. በክፍለ ከተማ ደረጃ የተመዘገቡ ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ያላቸው ቢያንስ 15 አሰልጣኞችና 15 ዳኞች መኖራቸው ሲረጋገጥ፣

7.3.3. በክፍለ ከተማ ደረጃ ስፖርቱ የሚዘወተርባቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በኪራይና በትውስት መኖራቸው ሲረጋገጥ ፣

7.3.4. የክፍለ ከተማ ስፖርት ፅ/ቤቶች በክፍለ ከተማ ደረጃ ስፖርቱን የሚመራ ኮሚቴ መቋቋሙን በፅሁፍ ሲያረጋግጡ፤

7.3.5. የስፖርት ማህበሩ ለመቋቋም ሦስት የክፍለ ከተማ ስፖርት ኮሚቴዎችና ክለቦች ወይም ፅ/ቤት ሲያረጋግጡ፤

7.3.6. በኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ማቅረብ ሲችል፡፡

7.3.7. የሂሳብ አያያዝን ሥርዓት የዘረጋ እና ኦዲትን በስራ ሊይ የሚያውል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

7.3.8. በግል ስፖርቶች በክፍለ ከተማ የተመዘገቡ ቢያንስ 150 ስፖርተኞች ሲኖራቸው፤

7.3.9. በአርት ስፖርቶች ቢያንስ በ2ኛ ዲን ደረጃ የሚያሰለጥኑ 5 የስልጠና ማዕከላት በክፍለ ከተማ ሲኖራቸው፤

7.3.10. ፅህፈት ቤት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ

7.4. ከተራ ቁጥር 4.1. — 4.3 እና በስራቸው በዝርዝር ያሉትን መስፈርቶች ያላሟሉ የስፖርት ማህበራት ፌዴሬሽን፣ አሶሴሽንና አደራጅ ኮሚቴ ሆነው አንድ የስፖርት ማህበር የሚያከናወናቸውን ተግባራት እያከናወኑ መቀጠል አለባቸው፡፡

7.5. ከተራ ቁጥር 4.1 — 4.3 እና በስራቸው በዝርዝር ያሉትን መስፈርቶች ያሟሉ ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶች የከተማ የስፖርት ማህበር ሆነው እንዲሰሩ ከሚመለከተው የስራ ክፍል ህጋዊ ፈቃድ ያገኛሉ፡፡

7.6. አንድ የከተማ ስፖርት ማህበር የሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበር ዕውቅና ለማግኘት ከወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ህጋዊ ዕውቅና ሰርተፍኬት ማረጋገጫ ሲሰጣቸው ብቻ ነው፡፡

7.7. በክፍለ ከተማ ደረጃ ያልተቋቋሙ የስፖርት ዓይነቶች በስፖርት ኮሚቴ ተደራጅተው የተሰጣቸውን ህዝባዊ ኃላፊነት መወጣት አለባቸው፡፡

## 8. የስፖርት ማህበሩ ስልጣንና ተግባር፤

8.1. የአደስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ምክር ቤት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤ ከመመሪያው ጋር የማይጣረስ የስፖርት ማህበሩን ልዩ ልዩ ደንብና መመሪያዎች ያወጣል፡፡

8.2. የስፖርት ቡድኖችና ክለቦች እንዲደራጅና እንዲጠናከሩ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣

8.3. ከስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳሬክቶሬት ህጋዊ ፈቃድ ተሰጧቸው የተመዘገቡ የስፖርት ክለቦችን ይመዘግባል፣ ደረጃቸውን ያወጣል፣ያወዳድራል፣

8.4. ከስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክቶሬትና ከሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ጋር በመተባበር ልዩ ልዩ የስፖርት ኮርሶችንና ስልጠናዎችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፡፡ በስራ ላይ ያውላል፡፡

8.5. ስፖርቱን በሚመለከት በአገር አቀፍ ፌዴሬሽን የፀደቁትን የአሰልጣኝነትና ዳኝነት ደረጃዎችን እንዲሁም የውድድር ህጎችንና ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣

8.6. ስፖርቱን በተመለከተ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣

8.7. ተተኪ ስፖርቶችን ለማፍራት የስልጠናና ውድድር ፕሮግራሞች እንዲተገበሩ ያደርጋል፣

8.8. የስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ያፀደቀውን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብና የስፖርተኞች የምዝገባ የዝውውር መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣

8.9. የስፖርት ቤተሰቦች የስፖርቱን ሕግና ደንብ እንዲያከብሩና ስፖርታዊ ጨዋነትን እንዲያጎለብቱ ተገቢውን ይፈፅማል፣

8.10. ስፖርቱን በሚመለከት በአገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ ጉባኤዎች፣ ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮችና አውደ ጥናቶች ላይ ይሳተፋል፣ ውሳኔዎችንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

8.11. ከስፖርት ፋሲሊቲ ተሳትፎና ውድድር ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲስፋፋ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣ በስፖርቱ የከተማዋና የስፖርት ማዘውተርያ ሥፍራ መረጃ ያደራጃል፤

8.12. ከስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር የስፖርት ትጥቆችና መሳሪያዎችን በሀገር ውስጥ በብዛትና በጥራት እንዲመረቱ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ጋር አስፈላጊውን ግንኙነት ይፈጥራል፤

8.13. ስፖርቱ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ለማድረግ የአጭር፣ መካከለኛ የረጅም ጊዜ ዕቅድ ይነድፋል፣ይተገብራል፣

8.14. ስፖርቱ በክፍለ ከተማዎች እንዲስፋፋና እንዲጠናከር የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል፣
8.15. ስፖርቱን በህብረተሰብ አቀፍ ፕሮግራሞች በት/ቤቶች፣ በመከላከያ ሰራዊት፣ በፖሊስ ሰራዊት፣ በፋብሪካ፣ ድርጅቶች፣ ወ.ዘ.ተ… እንዲስፋፋና እንዲታቀፍ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ያደረግል፣
8.16. ህዝባዊ ስፖርት ክለቦች እንደጠናከሩና እንዲቋቋሙ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈፅማል፣
8.17. ለስፖርተኞችና ለስፖርት ባለሙያዎች መብትና ጥቅምን ማስከበር ግዴታዎችንም እንዲወጡ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈፅማል፣
8.18. ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር የስልጠና፣የጥናትና ምርምር ስራዎች እንዲሰሩ ያስተባብራል፣
8.19. ከክፍለ ከተማ ስፖርት ምክር ቤቶችና ከስፖርት ፅ/ቤት ጋር በመተባበር ስፖርቱን የሚመሩ ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል፣
8.20. ስፖርቱን በሚመመለከት ከወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ ከክፍለ ከተማ ስፖርት ጽ/ቤቶችና ኮሚቴዎች እንዲሁም ከክልልና አገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፣
8.21. በከተማ ደረጃ በሚዘጋጁ ልዩ ልዩ ከተማ አቀፍ ውድድሮች፣ ፌስቲቫሎች፣ ኩነቶችና የወዳጅነት ውድድሮች ድጋፍ ይሰጣል፣
8.22. ከኮሚሽኑ ጋር በመተባበር ከተማ አቀፍ ባህሪይ ያላቸውን የስፖርት ውድድሮች በበላይነት ይመራል፣ከስፖርት ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር የአዲስ አበባን ምርጥ ቡድኖች ያዘጋጃል፣ ከስፖርት ፋሲሊቲ ተሳትፎና ውድድር ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ የስፖርት ውድድሮች እንዲሳተፉና ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
8.23. ከተማ አቀፍ ውድድሮች በክፍለከተማ ደረጃ እንዲዘጋጁ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።
8.24. ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ምክር ቤት ጋር በመሆን ከአቻ የሀገራት ከተሞች ጋር በውድድርና ስልጠና ግንኙነት ያደርጋል።
8.25. በስፖርቱ ዘርፍ የሙያ ማህበራት እንዲደራጅና እንዲጠናከር ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣
8.26. የስፖርት ማህበሩ በሰው ኃይል በፋይናንስ፣ በማቴሪያል ራሱን ችሎ እንዲደራጅ ተገቢውን ይፈጽማል፣ ራስን ለመቻል ገቢ ያመነጫል፣
8.27. በገቢ ማመንጫ ሥራ ላይ ለመሰማራት የስፖርት ማህበራት ዝርዝር ጥናትና ዕቅድ በማዘጋጀት በጠቅላላ ጉባኤዎቻቸው አቅርበው ማስጽደቅ ይኖርባቸዋል።
8.28. ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርበውና የሚፀድቀው የገቢ ማመንጫ ዕቅድ ማህበራት ከተቋቋሙበት ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያለውና የስፖርቱን ዓላማ የማይፃረር ሊሆን ይገባል።
8.29. ስፖርቱን የሚመለከቱ የተለያዩ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና የማሰራጨት
8.30. የሚመራውን ስፖርት በሚመለከት በሚቀርቡ ማናቸውም ክሶችና አቤቱታዎች ላይ ውሳኔ የመስጠት፤
8.31. ከአዲስ አበባ ስወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የተሰጠውን የፈቃድ የምስክር ወረቀት **በየዓመቱ** የማሳደስ፤

8.32. ስፖርት ማህበሩ የሚመራውን ስፖርት በተመለከተ ለተጫዋቾች የዝውውር እውቅና የመስጠት፣

8.33. ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ፤

8.34. በአለም አቀፍ ደረጃ የፀደቀውን እና ኢትዮጵያ የተቀበለችውን የፀረ- ዶፒንግ ኮንቬንሽን መሰረት በማድረግ የወጡ ህጎችን የማክበርና የማስከበር፤

8.35. ስፖርታዊ ጨዋነት እንዲሰፍን በስፖርታዊ መርሆዎችና ሥነምግባር ዙርያ ሥልጠና መስጠት፣ ስፖርታዊ ጨዋነት ሲጣስ እርምጃ መውሰድ፤

8.36. አጠቃላይ ዓመታዊ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክቶሬትና ለስፖርት ምክር ቤትያቀርባል፡፡

9. **አባልነት፤**

9.1. የአዲስ አበባ ------ ስፖርት ማህበር የኢትዮጵያ ________ስፖርት ማህበር አባል ይሆናል፤

9.2. የክፍለ ከተማ -------- ስፖርት ማህበር የአዲስ አበባ ከተማ _____ስፖርት ማህበር አባል ይሆናል፤

10. **ማንኛውም የስፖርት ማህበር አቋም፣**

**የስፖርት ማህበሩ፡-**

10.1. ጠቅላላ ጉባኤ፣

10.2. ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣

10.3. የተለያዩ ቋሚና ጊዛዊ ንዑሳን ኮሚቴዎች፣

10.4. በከተማ ደረጃ አንድ ፅ/ቤት ኃላፊ፣ በክ/ከተማና በወረዳ ስፖርት ፅ/ቤት የሚሰየም አንድ የስፖርት ባለሙያ

10.5. እንደአስፈላጊነቱ የቴክኒክ ባለሙያና ሌሎች ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

11. **ድምፅ በመስጠት የሚሳተፉ የስፖርት ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ አባላት፡፡**

11.1. የክፍለ ከተማ ስፖርት አሶሴሽኖች፣ ኮሚቴዎች ወይም ፌዴሬሽኖች ፕሬዝዳንት ወይም ስፖርት ምክር ቤት ተወካይ

11.2. ከስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ይሬክቶሬት እውቅና አግኝተው የተመዘገቡ የአዲስ አበባ ክለቦች /ቡድኖች/ አንድ አንድ ድምፅ፣

11.3. የስፖርት ማህበሩ ፕሬዚዳንትና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ሆኖም የስራ ጊዜያቸውን ጨርሰው አዲስ ምርጫ በሚያካሂድበት ጊዜ ግን ድምፅ አይኖራቸውም፤

12. **ድምፅ የማይሰጡ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት**

12.1. የሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበር ፕሬዚዳንት /ተወካይ

12.2. የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ተወካይና የስፖርት ማህበራት ማደራጃና ማልማት ዳይሬክቶሬት /ተወካይ

12.3. የፌዴሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ /ቴክኒካል ኦፊሰር

12.4. በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ ለስፖርቱ አስተዋፅኦ ያደረጉ ወይም በስፖርቱ የተለያየ አመራር በመስጠት ያገለገሉ የክብር አባላት

12.5. ጠቅላላ ጉባኤ የፈቀደላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች ቢበዛ አምስት፣

12.6. በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ ኦዲተር

12.7. አንድ የአሰልጣኞች ማህበር፣ የዳኞች ማህበር፣ የአትሌቶች /ስፖርተኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ፣

## 13.የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ዕጩ ስለማቅረብ

13.1. እያንዳንዱ የክፍለ ከተማ ስፖርት ኮሚቴ ወይም የስፖርት ምክር ቤት አንድ ዕጩ ለፕሬዚዳንት ሁለት ዕጩ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላሉ፣

13.2. የተመዘገቡና ድምፅ የሚሰጡ የከፍተኛ ክለቦች አንድ አንድ ዕጩ ለስራ አስፈፃሚ ያቀርባሉ

13.3. የሙያ ማህበራት ለስራ አስፈፃሚነት እጩ ማቅረብ ይችላሉ፣ ነገር ግን ሌላ ኃላፊነታቸው ከ3 ወር በፊት የመልቀቂያ ደብዳቤ ይዞ ሲቀርቡ ብቻ ይሆናል፡፡

13.4. የዕጩዎች አቀራረብ በፅሁፍ ማህተም የኃላፊው ፊርማ ያረፈበት ሆኖ ለስፖርት ማህበሩ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

13.5. የስፖርት ማህበሩ ዕጩዎቹን ህጋዊነት ካረጋገጠ በኋላ ከምርጫው 15 ቀናት በፊት ይፋ ያደርጋል፡ ሆኖም አከራካሪ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ህግ መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

13.6. ሴቶች 30 ፐርሰንት መወከል አለባቸዉ

## 14. ዕጩ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ብዛትና የምርጫ ሂደት

**14.1. ክፍለ ከተማዎችና ከፍተኛ ክለቦች ዕጩዎችን ያቀርባሉ፣ የፕሬዚዳንትና የስራ አስፈፃሚ ተለይቶ መቅረብ አለበት**

14.2. ለፕሬዚዳንት ከቀረቡት ዕጩዎች መካከል አንድ በጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣል፤ ለስራ አስፈፃሚ ከቀረቡት ዕጩዎች መካከል አራት/ስድስት/ስምንት አባላትና ሁለት ተጠባባቂ ይመረጣሉ፣

14.3. የፕሬዚዳንትም ሆነ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ ወይም በግልጽ እጅ በማውጣት ወይም በፅሁፍ ይሆናል፣

14.4. የስፖርት ማህበራት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ የሚከናወነው በአራተኛው ዓመት በሰኔ ወር መጨረሻ ይሆናል፡፡

14.5. በሀገር አቀፍና በሌላ ስፖርት ማህበራት ላይ በሥራ አስፈፃሚነት ያገለገሉ ሆነው ዕጩ ሆነው ሲቀርቡ ከነበሩበት ሥፍራ ምንያህል ዘመን በስራ አስፈፃሚ እንዳገለገሉ የሚገልጽ መልቀቂያ ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

14.6. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን ማብቂያው በየአራት ዓመቱ ስለሆነ በጉባኤው አስመራጭ ኮሚቴዎች ከ3 - 5 አባላት ያሉት ይዋቀራል፡፡

14.7. ም/ፕሬዝዳንትና ዓቃቤ ነዋይ ከተመረጡ አራት/ስድስት/ስምንት ዕጩዎች መካከል በግልጽ ወይም በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ በጠቅላላው ጉባኤ ይሰየማሉ፡፡

## 15.የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር፡-

15.1. በስፖርት ም/ቤት የፀደቁትን መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ የማሻሻያ ሃሳብ ያቀርባል፣

15.2. የስፖርት ማህበሩን የውስጥ መተዳደሪያ መመሪያዎችን ሌሎች ማስፈፀሚያ መመሪያዎች አውጥቶ ያፀድቃል ተግባራዊ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፣

15.3. የስፖርት ማህበሩን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይመርጣል፣ ይሽራል፣

15.4. ከስፖርት ማህበሩ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት መካከል አንድ ፕሬዝዳንት፣ አንድ ምክትል ፕሬዝዳንትና አንድ ዓቃቤ ነዋይ ይመርጣል፣

15.5. ስፖርቱ ስለሚስፋፋበት ሁኔታ ይመክራል ለስፖርት ም/ቤቱ ሀሳብ ያቀርባል፣

15.6. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተወሰኑ ከፍተኛ ቅጣቶችንና እገዳዎችን በመመርመር እንደ አስፈላጊነቱ በከፊል ወይም አጠቃላይ ምህረት ይሰጣል፣

15.7. የስፖርት ማህበሩን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት /ስትራቴጂያው/ ዕቅድ መርምሮ ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይገመግማል፣

15.8. የስፖርት ማህበሩን ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት ያፀድቃል፣

15.9. ዓመታዊ የስፖርት ማህበሩን የኦዲት ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፡፡

## 16. የስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የስብስባ ስነ-ስርዓት

16.1. የስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣

16.2. የስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ ወይም ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲጠይቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፣

16.3. በጉባኤው ወቅት ከግማሽ በላይ ወይም $50^{+1}$ የሆነ ድምፅ የሚሰጡ አካላት ከተገኙ ምልዕተ ጉባኤ ይሆናል፣

16.4. የውስጥ መመሪዎችን ለማፀደቅ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ለመምረጥ ወዘተ.... በመሳሰሉ ጉባኤዎች ላይ 2/3 አባላት መገኘት አለባቸው፣

16.5. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ምርጫ ሲደረግ የስራ ጊዜያቸውን የጨረሱ አባላት ድምፅ አይሰጡም፣

16.6. የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች የሚጸድቁት በግልፅ ድምፅ አሰጣጥ ሆኖ የሚለየው በድምፅ ብልጫ ነው፣

16.7. በጉባኤው ወቅት በአንድ ጉዳይ ላይ ድምፅ ለሁለት እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው የሚደግፈው ያልፋል፡፡

16.8. በ15 ቀን አንዴ ስራ አስፈጻሚዎች የሚገናኙ ሲሆን በተደጋጋሚ 3 ጊዜ ያለአግባብ የማይገኝ ስራ አስፈጻሚ ከአባልነት በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ሊሰናበት ይችላል

## 17.የስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ ጥንቅር፡-

17.1. የስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ አባላት ብዛት አምስት/ሰባት/ዘጠኝ ሆኖ የሚከተለው ጥንቅር ይኖረዋል

- አንድ ፕሬዝዳንት
- ተቀዳሚ ፕሬዘዳንት/እንደአስፈላጊነቱ/
- አንድ ምክትል ፕሬዝዳንት፣
- አንድ አቃቤ ነዋይ፣
- አራት /ስድስት/ ስምንት አባላት
- የፌዴሬሽኑ ፅ/ቤት ኃላፊ ወይም ቴክኒካል ባለሙያ ያለ ድምጽ፣

## 18.የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን፤

18.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን አራት ዓመት ይሆናል፤

18.2. አንድ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል መመረጥና ማገልገል የሚችለው በአንድ የስፖርት ማህበር ውስጥ ብቻ ነው፣

18.3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን አራት ዓመት ሆኖ የአገልግሎት ጊዜው በሰኔ ወር መጨረሻ ይጠናቀቃል፡፡ ብቃቱና ችሎታው እንዲሁም ፈቃደኝነቱ ተጠይቆ እንደገና በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ ብቻ መመረጥ ይችላል፡፡

## 19.የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት መምረጫ መመዘኛዎች

19.1. በዜግነት ኢትዮጵያዊ /ትውልደ ኢትዮጵያዊ/ የሆነ፣

19.2. ዕድሜው ከ 18 ዓመት በላይ የሆነ፣

19.3. የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆነ

19.4. ስፖርት ማህበሩን ለማገልገል ሙሉ ፈቃደኛ የሆነ፣
19.5. መልካም ስነ ምግባር ያለው፣ በጥሩ አርአያነት የሚጠቀስ ከፀረ-ስፖርት ድርጊትና ሱሶች ነፃ የሆነ፣
19.6. በህግ መብቱ ያልተገፈፈ
19.7. በሌሎች የስፖርት ማህበራት ወይምኮሚቴዎች ስራን በማዳከም ወይም ህግና ደንብ በመጣስ ከኃላፊነቱ ያልተነሳ፣
19.8. የአእምሮ ህመምተኛ ያልሆነ
19.9. ቢቻል አለም አቀፍ ተምክሮ ያለዉ
19.10. ስፖርቱን በሀብቱ በእውቀቱና በሙያዉ ማገዝ የሚችል
19.11. ነዋሪነቱ በሀገር ዉስጥ የሆነ
19.12. ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰዉ በፕሬዘዳንትነት ወይም በምክትል ፕሬዘዳንትነት ሊመረጥ አይችልም
19.13. የተመረጠ ማንም የስራ አስፈጻሚ አመራር 4 አመት አገልግሎቱን ሳይጨርስ በስራ ላይ እያለ በሌሎች ፌዴሬሽኖችና በሀገር አቀፍ ደረጃ ባሉ ፌዴሬሽኖች እጩ ሆኖ መቅረብ አይችልም
19.14. በአሰልጣኝነት፣ በዳኝነት፣ በክለብ ቡድን መሪነት ፣ ያሉ የስፖርት ባለሙያዎች በስራ አስፈፃሚና በንዑስ ኮሚቴነት ተመርጠው ማገልገል አይችሉም፣
19.15. በመንግስት ስፖርት አደረጃጀቶች/በሀገር አቀፍና በከተማ/ ወይም በአገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ሰራተኛ ከሆነ መወዳደር አይችልም
19.16. የዶፒንግ የህግ ጥሰቶችን የፈጸመ ከሆኖ
19.17. በማንኛዉም ስፖርት ማህባር በስራ አስፈጻሚነት አገልግሎ የስራ ዘመኑን ያጠናቀቀ ከሆነ ወይም
19.18. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል በመሆን በገዛ ፍቃዱ ከአባልነት እንዲነሳ የጠየቀ ከሆነ በዚያዉ ምርጫ ዘመን በሌላ ስፖርት ማህበር የስራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ ሆኖ መመረጥ አይችልም፡፡

## 20. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

20.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 21 የተጠቀሱትን ሁሉ ተግባራዊ ያደርጋል፣
20.2. የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣
20.3. የስራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣
20.4. ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣
20.5. ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ቋሚና ጊዜያዊ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ተግባራቸውን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣ የስራ ጊዜያቸውንም ይወስናል፣
20.6. ልዩ ልዩ የውስጥ መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣
20.7. ለስፖርት ማህበሩ አስተዳደርና አመራር ውድቀት በግልና በጋራ ተጠያቂ ይሆናል፣
20.8. ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት መካከል በተለያየ ምክንያት ከተሰናበቱ በተጠባባቂነት ከተመረጡት ሁለት አባላት መካከል እንደ ድምፅ ቅደም ተከተላቸው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ወዲያውኑ መተካት ይችላል፡፡ ሆኖም በሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያፀድቃል፣

20.9. ለስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክቶሬት ከክፍለ ከተማ ስፖርት ፅ/ቤት ስፖርት ምክር ቤት ጋር በመተባበር ስራውን ያከናውናል፣

20.10. በሚቀርቡ የውድድር ክለቦችና አቤቱታዎች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

20.11. የስፖርት ውድድሮች መግቢያ ትኬት ዋጋ ተመን ይወስናል፣

20.12. በከተማው የተዘረጋውን የታዳጊ ወጣቶች የስፖርት ስልጠና ልማት ፕሮግራም በተጠናከረ መልኩ እንዲካሄድ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ በራሱም አደራጅቶ ይመራል፤

20.13. የስፖርት ማህበሩ የገቢ ምንጭ በቋሚነት እንዲያድግ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈፅማል፣

20.14. የስፖርት ማህበሩ ፋይናንስና ንብረት ያስተዳድራል፣ ይፈቅዳል፣ በስፖርት ምክር ቤት ደንብና መመሪያ መሰረት በጋራ እየወሰነ በፅቅድ ለተያዙ ስራዎች እንዲውል ያደርጋል፣

20.15. በውሳኔዎች የጋራና የግል ተጠያቂነትና ኃላፊነት ይወስዳል፣

20.16. የማህበሩ ጸሀፊ የጽ/ቤቱን ሰራተኞች የመቅጠርና ያሰናብታል

20.17. የክብር አባላትን በመለየት በጠቅላላ ጉባኤ ያጸድቃል

20.18. ፕሬዝዳንቱና ም/ፕሬዘዳንቱ በሌሉበት ጊዜ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መካከል አባል የእለቱን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ይመራል፣

**21.የስፖርት ማህበሩ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ ስነ-ስርዓት፣**

21.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ በ15 ቀን አንድ ጊዜ ይደረጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከዚያ ባነሰ ጊዜ ሊደረግ ይችላል፣

21.2. በስብሰባው ወቅት ከግማሽ በላይ የሆኑ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፣

21.3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ የሚፀድቀው በድምፅ ብልጫ ነው፣

21.4. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ በአንድ ጉዳይ ላይ በድምፅ ለሁለት እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው የሚደግፈው ያልፋል፣

**22.የስፖርት ማህበሩ ፕሬዝዳንት ስልጣንና ተግባር፣**

22.1. በማንኛውንም ስፍራ የስፖርት ማህበሩ ሕጋዊ ተጠሪ ይሆናል፣

22.2. የስፖርት ማህበሩን ገንዘብ ከፅ/ቤቱ ኃላፊ፣ ፋይናንስ ባለሙያ ወይም ዓቃቢ ንዋይ በጋራ በመሆን እንዲንቀሳቀስ ይወስናል። አፈፃፀሙን ይከታተላል። የወጡ ወጪዎች በቃለጉባኤ እንዲደግፍና በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲፀድቅ ያደርጋል፣

22.3. የጠቅላላ ጉባኤውንና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ስብሰባዎች ይመራል፣ ድምፁ እኩል ሲሆን ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣

22.4. የጠቅላላ ጉባኤውንና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎችን በትክክል መከናወናቸውን ያረጋግጣል።

22.5. አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ከም/ፕሬዘዳንቱና ከአቃቢ ነዋዩ ወይም ከፅ/ቤት ኃላፊ ጋር ውሳኔ ሰጥቶ ጉዳዩን በሚቀጥለው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ አቅርቦ ያፀድቃል፣

**23. የም/ፕሬዘዳንቱ ስልጣንና ተግባር**

23.1. ፕሬዘዳንቱ በማይገኝበት ጊዜ ሁሉ እርሱን ተክቶ ይሰራል፣

23.2. የፕሬዝዳንቱ የቅርብ ረዳት ሆኖ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈፅማል፣

23.3. ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ወቅት የስፖርት ማህበሩን ገንዘብ ከፅ/ቤቱ ኃላፊ፣ ፋይናንስ ባለሙያ ወይም ዓቃቢ ንዋይ በጋራ በመሆን እንዲንቀሳቀስ ይወስናል።

አፈፃፀሙን ይከታተላል።የወጡ ወጪዎች በቃለ-ጉባኤ እንዲደገፍና በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲፀድቅ ያደርጋል፣

23.4. ፕሬዘዳንቱ በማይገኝበት ጊዜ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ከአቃቢ ነዋዩና ከአንድ ስራ አስፈፃሚ አባል ጋር ውሳኔ ሰጥቶ ጉዳዩን በሚቀጥለው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ላይ አቅርቦ ያፀድቃል፣

23.5. **ፕሬዝዳንቱና ም/ፕሬዘዳንቱ በሌሉበት ጊዜ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መካከል አባል የእለቱን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ይመራል፣**

**24.የስፖርት ማህበሩ ጽ/ቤት ኃላፊ ስልጣንና ተግባር፣**

ተጠሪነቱ ለስፖርትማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክቶሬት ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

24.1. የስፖርት ማህበሩን ጽ/ቤት ይመራል፣ እንዲሁም ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ተግባራት ሁሉ ያከናውናል፣

24.2. የስፖርት ማህበሩን የአስተዳደርና የፋይናንስ ንብረት እንዲሁም የቴክኒክ ተግባሮች ይከታተላል፣

24.3. ከፕሬዝዳንቱ ወይም ም/ፕሬዝዳንቱ፣ ከፋይናንስ ባለሙያ ወይም ዓቃቤ ነዋይ ጋር በመሆን በስራ አስፈፃሚው ውሳኔ መሰረት የስፖርት ማህበሩን ገንዘብ ያንቀሳቅሳል፣ በቼክ ላይም ይፈርማል፣

24.4. የስፖርት ማህበሩን የፋይናንስ ንብረት በስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት መንቀሳቀሱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

24.5. የስፖርት ማህበሩ የአገር ውስጥና የአቻ ከተሞች ግንኙነቶችና የጽሁፍ ልውውጦች በፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ያከናውናል፣

24.6. ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴንና የንዑሳን ኮሚቴዎችን ውሳኔ ተግባራዊ ያደርጋል፣

24.7. የስፖርት ማህበሩን /የፌዴሬሽኑን ጉባኤውንና የስብሰባ አጀንዳዎች ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ የስብሳበ ጥሪ ያስተላልፋል፣ ቃለ-ጉባኤዎችና ሰነዶች በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣

24.8. የስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በደንብና መመሪያ መሰረት መከናወናቸውን ይከታተላል፣

24.9. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ዓመታዊ ዕቅድና በጀት አንዲሁም የስራ አስፈፃሚ ሪፖርት ለስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክቶሬትና ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፣

24.10. የድጋፍ ጥያቄዎችን፣ የፋይናንስ ጉዳዮች በስራ አስፈፃሚ እውቅና ብቻ ይፈፀማል፣

**25.የስፖርት ማህበሩ ቴክኒካል ባለሙያ ስልጣንና ተግባር**፣ ተጠሪነቱ ለፌዴሬሽኑ ፅ/ቤት ኃላፊ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

25.1. የስፖርት ማህበሩን የቴክኒክ ኮሚቴ በፀሀፊነት ይመራል

25.2. የስፖርት ማህበሩን የቴክኒክ ተግባሮች ይከታተላል፣

25.3. የስፖርት ማህበሩ ችግሮችን በመለየት የጥናት ኮሚቴን በማዋቀር በስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ችግር ፈቺ ጥናት ያከናውናል፣

25.4. የስፖርት ማህበሩን የውድድርና የስልጠና መረጃዎች በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፣ይቆጣጠራል፣

25.5. በስፖርት ማህበሩ፣በከተማ ደረጃና በስፖርት ማዕከላት የተቋቋሙ የታዳጊ ወጣቶች የስፖርት ስልጠና ፕሮግራምን ኮሚቴ እንዲደራጅ በማድረግ ይከታተላል፣ ቴክኒካል አፈፃፀሙን ይገመግማል፤

25.6. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን የሚሰጡትን ተግባራት ሁሉ ያከናውናል፣

## 26. የዓቃቤ ነዋይ ስልጣንና ተግባር

26.1. የማህበሩን ፋይናንስ በደንቡ መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

26.2. የስፖርት ማህበሩን ንብረት በአግባቡ ገቢና ወጪ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

26.3. ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርብውን የስፖርት ማህበሩን በጀት ይገመግማል፣ ማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል። የስፖርት ማህበሩን በጀት አዘጋጅቶ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣

26.4. ለጠቅላላ ጉባኤ አጠቃላይ የፋይናንስ ንብረት ኦዲት ሪፖርት ያቀርባል፣

## 27. የፋይናንስ ባለሙያ ስልጣንና ተግባር

27.1. የማህበሩን ፋይናንስ በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

27.2. የስፖርት ማህበሩን ሂሳብ በአግባቡ ገቢና ወጪ ሰነዶች ይይዛል፣ ያደራጃል፣ በተጨማሪም ቼክ ያዘጋጃል፣ በቼክ ላይም ይፈርማል፣

27.3. ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርብ አጠቃላይ የፋይናንስ ሪፖርት ለዓቃቤ ነዋይ ይሰጣል፣

## 28. ስለ ንዑሳን ኮሚቴ መቋቋምና የስራ ዘመን

28.1. የስፖርት ማህበሩ ተግባርና ኃላፊነቱን በሚገባ ለመወጣት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ቋሚና ንዑሳን ኮሚቴዎች ያቋቁማል፣

28.2. የንዑሳን ኮሚቴ የስራ ዘመን አራት ዓመት ሆኖ የአገልግሎት ጊዜው በሰኔ ወር መጨረሻ ይጠናቀቃል። ብቃቱና ችሎታው እንዲሁም ፈቃደኝነቱ ተጠይቆ እንደገና በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ ብቻ መመረጥ ይችላል።

28.3. **ንዑሳን ኮሚቴዎች የስራ ዘመን በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች የስራ ዘመን ይሆናል፣**

28.4. የንዑሳን ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች እንደ አስፈላጊነቱ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አካላት መካከል ይሆናሉ፣

28.5. የንዑሳን ኮሚቴ አባላት ብዛት እንደ ስራ እንቅስቃሴው ከ3 - 5 ድረስ ሊሆን ይችላል፣

28.6. አንድ የንዑስ ኮሚቴ አባል መመረጥና ማገልገል የሚችለው በአንድ የስፖርት ማህበር ውስጥ ብቻ ነው።

## 29. አባልነት

29.1. የስፖርት ማህበሩ የክፍለ ከተማ የስፖርት ምክር ቤቶችን ኮሚቴዎችንና የስፖርት ክለቦችን አባል አድርጎ ይመዘግባል።

## 30.የአባላት መብትና ግዴታ

30.1. የስፖርት ማህበሩ መቋቋሚያና መተዳደሪያ መመሪያ ከሌሎች የስፖርት ማህበራት የሚመራባቸውን የስፖርት ህግና ደንቦች ማክበርና መፈፀም፣

30.2. የስፖርት ማህበሩ በሚያዘጋጃቸው ከተማ አቀፍ ውድድሮች መሳተፍ፣

30.3. የስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የመምረጥና የመመረጥ መብት ማግኘት፣

30.4. የከተማው ስፖርት ማህበር ስፖርቱን ለማሳደግና ለማስፋፋት በሚያደረገው የልማት እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ፣

30.5. የስፖርት ማህበሩ በስፖርት ምክር ቤቱ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ስራውን ተግባራዊ ያደርጋል፣

## 31.የፋይናንስና ንብረት አጠቃቀም፤

31.1. ስፖርት ማህበሩ የራሱ ባንክ አካውንት ይኖረዋል። ሆኖም ሁኔታዎች ተሟልተው የራሱ አካውንት እስኪኖረው ድረስ ሂሳቡ በስፖርት ም/ቤቱ አካውንት በአደራ ይቀመጣል፣

31.2. የራሳቸው የባንክ አካውንት ያላቸው የስፖርት ማህበራት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወስነው መሰረት ገንዘብ በስፖርት ማህበሩ ፕሬዝዳንት ወይም ም/ፕሬዝዳንት፣ ዐቃቤ ነዋይና ፅ/ቤት ኃላፊ የተረጋገጠና ያፀደቀው አካል ፈርሞበት በስፖርት ም/ቤቱ በተመደቡ ወይም በማህበሩ በተቀጠሩ ፋይናንስ ባለሙያዎች ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ያደርጋል፣

31.3. ለስፖርት ማህበሩ እንቅስቃሴ ከስፖርት ም/ቤቱ የሚሰጠው የበጀት ድጋፍ ድጎማ እንዲሁም ማናቸውም በድጋፍ የሚገኙ ገቢዎች በስፖርት ማህበሩ የባንክ ሂሳብ ወይም በስፖርት ም/ቤት አካውንት ገቢ መደረግ አለበት፣

31.4. ማንኛውም ገንዘብና ንብረት ገቢ ወጪ የሚሆነው ስፖርት ም/ቤቱ ባሳተመው የፋይናንስ ንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች ብቻ ሲሆን እያንዳንዱ የስፖርት ማህበር ስፖርት ም/ቤቱ የሚያሳትመውን ደረሰኝ ከኮሚሽኑ በግዢ መውሰድ ይኖርበታል፣

31.5. ለጥቃቅን ወጪዎች የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን /ፒቲ ካሽ/ በስፖርት ምክር ቤቱ ደንብ መሰረት በተመደበላቸው የፋይናንስ ባለሙያ እጅ ይቀመጣል፣

31.6. በኮሚሽኑ የተመደበው ገንዘብ ያዥ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተወሰነውን ፒቲ ካሽ በስፖርት ም/ቤቱ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ያንቀሳቅሳል።

31.7. የስፖርት ማህበሩ ፅ/ቤት ኃላፊ በስፖርት ም/ቤቱ የተወሰነውን ፒቲ ካሽ በፋይናንስ መመሪያ መሰረት ይመራል፣

31.8. የስፖርት ማህበሩ ፌደሬሽን ፅ/ቤት ኃላፊ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተወሰነውን ንብረት፣ በስጦታ የተሰጠም ሆነ በግዢ የተፈፀመ በስፖርት ምክር ቤት የፋይናንስና ንብረት መመሪያ መሰረት ገቢ ወጪ ሆኖ ይንቀሳቀሳል፣

31.9. የስፖርት ማህበሩ ንብረት ከመንግስት በተመደበው ፌደሬሽን ፅ/ቤት ኃላፊ /ህጋዊ ቅጥር በተፈፀመለትና በቂ ዋስ ባለው ሰራተኛ እጅ ብቻ ርክክቡ ይፈፀማል፤

31.10. ራሳቸውን ያልቻሉ የስፖርት ማህበራት ሙሉ ለሙሉ ራሳቸውን ችለው እስኪወጡ ድረስ ገንዘብ ያዥና ሂሳብ ሹም በፑል ይመደባል፣

31.11. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የስፖርት ማህበሩ ገንዘብ አሰባሰብና አወጣጥ በአብዛኛው ቅድሚያ ሊሰጣቸው ለሚገባ የልማት እቅዶች እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣

31.12. ለተለያዩ ጉዳዩች ወጪ የሆነ የስፖርት ማህበሩ ገንዘብ ቢበዛ ስራው ባለቀ በ7 ቀናቶች ውስጥ ማወራረድ አለበት፣

31.13. የማህበሩ ጸሀፊ የጽ/ቤቱን ሰራተኞች የመቅጠርና ያሰናብታል

## 32. ስለ ሂሳብ ምርመራ

32.1. የስፖርት ማህበሩ ሂሳብ በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች ወይም ስፖርት ም/ቤቱ በሰየማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ እየተመረመረ በስፖርት ማህበሩ ጠ/ጉባኤ ይቀርባል አጠቃላይ የኦዲት ሪፖርቱ ለጠየቀው አካል /ለዳይሬክተሩ/ብቻ በጽሁፍ ይቀርባል።

## 33. ራስን በራስ ማስተዳደር ስለመቻል

33.1. አንድ ከተማ አቀፍ የስፖርት ማህበር /ፌዴሬሽን/ ራስ በራስ የማስተዳደር መብት አለው፣

33.2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ድንጋጌ ቢኖረውም አንድ ከተማ አቀፍ የስፖርት ማህበር /ፌዴሬሽን ራስን በራስ ማስተዳደር የሚችለው፡-

- የራሱ የሆነ ፅ/ቤት ሲኖረው ወይም በኪራይ ወይም በስጦታ መሆኑን ማረጋገጫ የሚያመጣ፣
- የሚጠቀምበት የራሱ የሆነ ካርታ ያለው ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ካልሆነም በትውስት፣ በኪራይ ሲኖረው
- **ቢቻል** ቋሚ የገቢ ምንጭ ሊኖረው ይገባል፣

33.3. ራሱን ለማስተዳደር ጥያቄ ያቀረበው የስፖርት ማህበር /ፌዴሬሽን ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች በበቂ ሁኔታ መሟላቱ ሲረጋገጥ በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ና የከተማ አስተዳደር ስፖርት ም/ቤት ራሱን እንዲያስተዳድር ሊፈቅድለት ይችላል፣

33.4. የስፖርት ማህበሩ /ፌዴሬሽኑ ራሱን እንዲያስተዳድር በተፈቀደለት ጊዜ የስፖርት ም/ቤቱ የሀገሪቱን /አስተዳደሩን/ የስፖርት ፖሊሲ ህጎች፣ ደንቦችን መመሪዎችን አክብሮ መስራቱን በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ድጋፍና ክትትል ይደረግለታል፣

**30 .የተከለከለ ተግባር**

30.1. ማንኛውም የስፖርት ማህበር /ፌዴሬሽን/ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በጎሳና በዘር መደራጀት በዚህ ሁኔታ የተደራጁትን ክለቦችን ተቀብሎ ዕውቅና መስጠት አይችልም፣

30.2. የስፖርት ማህበሩ /ፌዴሬሽኑ/ አባል በተለያዩ ጉዳዮች የተወሰዱትን ገንዘብ ሳያወራርዱ ሌላ ገንዘብ በስማቸው ወጭ አድርጎ መስጠት አይቻልም፣

30.3. የስፖርት ማህበሩ /ፌዴሬሽኑ/ የስራ እንቅስቃሴ በግል ፖ.ሣ.ቁ. ፋክስ ኢሜል አድራሻ መጠቀም አይችልም፡፡ የስፖርት ማህበሩ /ፌዴሬሽኑ የራሱ የመልዕክት አድራሻ ከሌለው በኮሚሽኑ የመልዕክት አድራሻ መጠቀም ይኖርበታል፣

30.4. አንድ ሰው በስራ አስፈፃሚ ወይም በቋሚ ኮሚቴ አባልነት ሊያገለግል የሚችለው በአንድ የስፖርት ዓይነት በአንድ ክለብ ወይም ከተማ አቀፍ የስፖርት ማህበር /ፌዴሬሽን/ ብቻ ነው፣

30.5. በየደረጃው የሚገኙ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ የክፍለ ከተማና የወረዳ ስፖርት ዘርፍ ቋሚ ሰራተኞች የስፖርት ማህበር /ፌዴሬሽን/ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ንዑሳን ኮሚቴ አባል ሆነው መመረጥ አይችሉም፣

30.6. የከፍተኛ ክለቦችን በመወከል በከተማ አቀፍ የስፖርት ማህበር /ፌዴሬሽን/ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ንዑሳን ኮሚቴ አባል ሆኖ የተመረጠ የክለብ አመራር በራሱ ክለብ አባል ሆኖ መቀጠል አይችልም፣

30.7. ማንኛውም ስፖርት ማህበር ምንም አይነት ምዝገባ ሳያደርግና ዕውቅና ሳይሰጠው መንቀሳቀስ አይችልም፣

30.8. በግልም ሆነ በቡድን በማንኛውም የስፖርት ዘርፍ ወይም በማህበርና በድርጅት ተደራጅተው መንግስት የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎችና ህጎች እንዲሁም ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ  የሚያወጣቸውን መመሪያዎች መጣስ ወይም መተግበር ላይ ለማዋል ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘት፣

30.9. በስፖርት ማህበር /ፌዴሬሽን አሰራር ውስጥ አንድ ሰው ገንዘብ ወይንም ንብረት ራሱ ጠያቂ ራሱ አፅዳቂ በመሆን ገንዘብና ንብረት ማንቀሳቀስ አይችልም፡፡

30.10. እድሳት ሳያደርጉ የትኛዉንም ስፖርታዊ ፕሮግራም ማከናወንና መሳተፍ

30.11. የጸረ አበረታች ቅመሞች ድንጋጌዎችን መጣስ፣

30.12. የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚጻረሩ ተግባራ መፈጸም

30.13. ይህን መመሪያ የሚጻረሩ ደንብ ማዉጣት

30.14. በየትኛዉም መንገድ አገልግሎቱን ያልጨረሰ ስራ አስፈጻሚ ለብሄራዊ ፌዴሬሽን እጩ ሆኖ አይላክም

30.15. በማንኛዉም ስፖርት አይነት አንድ ሰዉ ሁለት ቦታ አመራር ሆኖ መምራት አይችልም

30.16. የክለብ ቡድን መሪ፣ ከለብ ያለዉ፣ አሰልጣኝ በተመሳሳይ ስፖርት አይነት ተመርጠዉ ማገልገል አይችሉም

**31 የመተባበር ግዴታ:-**

31.1. የተለያዩ ችግሮች ሲከሰቱና በስፖርት ማህበራት መካኮል ለሚነሳው ክርክር ምክንያት ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ወይም የአስተዳደሩ ስፖርት ም/ቤት ሠነዶችንና ዶክመንቶችን ማስመርመር ሲፈልግ ፌዴሬሽኑ /ማህበሩ/ የመተባበር ግዴታ አለበት፣

31.2. ማንኛውም አባል ፌዴሬሽኑን በመወከል በአገር አቀፍ ስብሰባዎች ከተሳተፉ በኋላ በፌዴሬሽኑ ስም የተላኩትን ሰነዶችና ዶክመንቶች እጅግ ቢዘገይ በሰባት ቀናት ውስጥ ለፌዴሬሽኑ /ለማህበሩ/ ፅ/ቤት የማስረከብ ግዴታ አለበት፣

**32 ፆታን በተመለከተ**

⇒ በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀ በሙሉ ሴቶችንም ያጠቃልላል፡፡

**33 ኃላፊነትን ስለ አለመወጣት፤**

33.1. የስፖርት ማህበሩ /ፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ኃላፊነቱን በሚገባ ሳይወጣ ሲቀር የስፖርት ምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጉዳዩን አጣርቶ ወዲያውኑ ጠቅላላ ጉባኤ አስጠርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፣

**34 ቅጣት**

⇒ ይህንን መመሪያ የጣሰ ወይም የዚህን ደንብ አፈፃፀም ያሰናከለ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ይቀጣል፡፡ ፌዴሬሽኑም የስነ- ስርዓት እርምጃ መውሰድ ይችላል፡፡

⇒ የዚህ መመሪያ **አንቀፅ 30.1 እና 30.2** የተዘረዘሩትን የተላለፈ ማንኛውም የከተማ ፌዴሬሽን፡-

ሀ. በመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ከወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ይሰጠዋል፣

ለ. በ "ሀ" በተገለፀው መሰረት ካልታረሙ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ተጠርቶ ውሳኔ እንዲተላለፍ ይደረጋል፣

ሐ. በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ካልታረሙ ፌዴሬሽኑ ከእንቅስቃሴ ታግዶ ሌላ ምርጫ ይካሄዳል፣

መ. ማንኛውም የስፖርት ማህበራት የሚወጡ መመሪያዎች ወይም ደንቦች ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሆኖ ከተገኙ ቢሮዉ ወዲያውኑ የሚቃረነውን የህግ ድንጋጌ እንዲስተካከል በጽሑፍ ያሳውቃል፣ ማህበሩ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ተቀብሎ ካላስተካከለ ቢሮዉ መመሪያው ወይም ደንቡ ስራ ላይ እንዳይውል ያግዳል

**35 ስለማሻሻል፤**

⇒ ይህንን መመሪያ ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት **2/3ኛው** እንዲሻሻል ሲስማማበት ለከተማው ስፖርት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ቀርቦ ሲታመንበት ሊሻሻል ይችላል፡፡ በተጨማሪም የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በስፖርት ም/ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡ በስፖርት ም/ቤት ጠ/ጉባዔ ሲፀድቅም ተግባራዊ ይሆናል፡፡

36 ስለስፖርት ማህበራት ምዝገባና ዕውቅና ማግኘት

36.1 ማንኛዉም የስፖርት ማህበር በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን በማሟላት መመሪያዉ በወጣ ሶስት ወራት ጊዜ ዉስጥ ዳግም ምዝገባና ይውቅና ሰርተፍኬት ማግኘት አለባቸዉ

36.2 ከተማ አቀፍ ደረጃ ከዚህ በፊት ያልተመዘገቡና እውቅና ያላገኙ የስፖርት ማህበር በዚህ መመሪያ ዉስጥ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች አመልቶ ሲገኙ ፍቃድ ይሰጣቸዋል

36.3. ቀደም ሲል በከተማ አቀፍ ደረጃ ተደራጅተዉ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ የስፖርት ማህበራት የተቀመጡትን መስፈርት አሟልተዉ ካልተገኙ ስያሜቸዉን እንደያዙ እስከ አራት አመት ድረስ የማደራጀት ጊዜ ይሰጣቸዋል

3.6.4. ማንኛውም የስፖርት ማህበራት ዳግም ምዝገባ ሲቀርብ በስሩ የተደራጁ ክለቦች ስያሜ፣ አርማና፣ መዝሙራቸው ከብሔር፣ ከፖለቲካና ከሃይማኖት ነፃ አዴርገው መቅረብ አለባቸው፡፡

36.3 የስፖርት አሶሴሽኖች የፌዴሬሽን መስፈርት ሲያሟሉ የቀድሞ ስማቸውን ይዘው በፌዴሬሽን ደረጃ አድገው መመዝገብ ይችላሉ፡፡

37. የፍቃድ ዕዴሳት

37.1. ማንኛውም ከተማ አቀፍ ስፖርት ማህበር የፍቃድ ምስክር ወረቀት በየአራት ዓመቱ ለቢሮዉ አቅርቦ ማሳደስ አለበት፡፡

37.2. ማንኛውም ከተማ አቀፍ ስፖርት ማህበር ዕድሳት ለማድረግ የማህበሩን የፋይናንስ ሪፖርት፣ ኦዲት ሪፖርት፣ የጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርትና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ዝርዝርና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች ለቢሮዉ ማቅረብ ይጠበቅበታል

37.3. በተሰጠው አራት ዓመት የማደራጃ ጊዜ የሚጠበቅበትን መስፈርት ማህበሩ ካላሟላ አከተማ አቀፍ የሚለውን ስያሜ በመተው በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚንቀሳቀስ ይሆናሌ፡፡

37.5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 37.2 የተጠቀሱትን መረጃዎች አሟልቶ ያልተገኘ የስፖርት ማህበር እድሳት አይደረግለትም፡፡

38. የተሻረ መመሪያ

⇒ በ2012ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የወጣው የስፖርት ማህበራት መቋቋሚያና መተዳደርያ መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

39. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ፤

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ም/ቤት 22/03/2015 ዓ/ም ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## አቶ በላይ ደጀን

## የአዲስ አበባ ስፖርት ምክር ቤት ም/ሰብሳቢ